# በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## ÄTHIOPISCH-ORTHODOXE KIRCHE IN DEUTSCHLAND

Ückeratherstr. 2,D-50739 Köln
Tel/ Fax: 0221/ 599 2623
E-mail:aeokd@gmx.de
www.aethiopisch-orthodoxe-kirche-deutschland.de

*„በእውነት ጽሑፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ፤ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር  ማንም የሚያጽናናኝ የለም።“ ዳን. ፲.፳፩*

*የተወደዳችሁ ምእመናንና ምእመናት!*

የዚህ ዓመት የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል በዓለ ንግሥ  ሰኔ ፱ እና ፲ ቀን ፳፻፬ ዓ ም ( 16./17.06.2012) በኮለኝ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ይከበራል።

ሰለዚህ በቦታው ተገኝታችሁ የክብረ በዓሉና የሰአሌ ምሕረት የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል የበረከቱ  ተካፋዮች ትሆኑ ዘንድ በአክብሮት ተጋብዛችኋል።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

ሊቀ ካህናት ዶ/ር  መርዓዊ ተበጀ

## መ ር ሃ  ግ ብ ር

<u>ሰኔ ፱ ዕለተ ቀዳሚት ፳፻፬ ዓ ም (16**Juni 2012**)</u>  ከማታው ፲፪ (18. 00 Uhr Vesper) የዋዜማ ጸሎት ከደረሰ በኋላ ትምህርተ ወንጌል ይሰጣል። ቀጥሎም የተለያዩ ጣዕመ  ዝማሬ  ያላቸው መዝሙሮች በሰንበት ት/ቤት መዘምራን ቀርበው እንዳበቁ፤ ለተሳላሚዎች ራት ይቀርባል።

<u>ሰኔ ፲ ዕለተ እሑድ ፳፻፬ ዓ ም   **(17. Juni 2012)**</u>  ከንጋቱ  ፲፩ ሰዓት ላይ (5.00 Uhr) ጸሎተ ዕጣን ተደግሞ የዕለቱ ስብሐተ  እግዚአብሔር  ይደርሳል። ከጧቱ ፪(8) ሰዓት ላይ ሥርዓተ  ቅዳሴው ተጀምሮ እንዳበቃ  ሥርዓተ ዑደት  ይካሄዳል። ማኅሌታዊ  ሽብሸባ  በተለያዩ  የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ቀርቦ  ታቦተ  ሕጉ  ወደ መንበሩ  እንደተመለሰ፤ ለበዓሉ  ከምእመናን የተዘጋጀው ምሳ ከበጋ ባዛርና ከቡና ማፍላት ሥነ ሥርዓት ጋር ይቀርባል።